በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል አሥራ አንድ

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፲፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

***<u>ቅጣታቸውንም በመቀበል…</u>***

5. *<u>ተግሳጽ ከጥፋትና ከውድቀት ይታደጋል</u>*

- በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ተግሣጽን የሚጠብቅ በሕይወት መንገድ ይሄዳል ዘለፋን የሚተው ግን ይስታል።›› *<u>ምሳ 10፡17</u>*፡፡ ተብሎ እንዲሁም በልበ አምላክ ዳዊት ደግሞ ‹‹መገሠጽስ እግዚአብሔር ገሠጸኝ ለሞት ግን አልሰጠኝም።›› *<u>መዝ 117(118)፡18፡፡</u>* በማለት ተነግሮናል፡፡
- ልበ አምላክ ዳዊት እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ ለሞት አሳልፎ ሊሰጠው እንዳልፈቀደ በመረዳት በእግዚአብሔር ተግሳጽ ደስ ተሰኝቶ ዘምሯል፡፡
- ጠቢቡ ሰሎሞንም ‹‹ክፉ መቅሠፍት መንገድን በተወ ሰው ላይ ይመጣል፥ ዘለፋንም የሚጠላ ይሞታል።›› *<u>ምሳ 15፡10፡፡</u>* በማለት በጻፈልን የጥበብ ቃል አባታቸው ካህኑ ዔሊ ስላልገሰጻቸው የጠፉትን ልጆቹን እንመለከታቸዋልን፡፡ *<u>ቀዳ ሳሙ ምዕራፍ 2 እስከ ምዕራፍ 6፡፡</u>*
- የተወደዳችሁ ወገኖቼ! ተግሳጽን በምን በኩል ቢመጣባችሁ ትቀበሉታላችሁ? ተግሳጽንስ ትወዱታላችሁ? ወይስ ትጠሉታላችሁ? ትቀበሉታላችሁ? ወይስ ንቃችሁ ትተውታላችሁ? ታደንቁታላችሁ? ወይስ ትንቁታላችሁ?
- ከሚገስጿችሁ ሰዎችስ ጋር ያላችሁ ግኑኝነት ምን ይመስላል? በፍቅርና በመታዘዝ ላይ የተመሠረተ ወይስ በጥላቻና በማግለል?

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ቅጣታቸውንም በመቀበል...***

## 5. ተግሳጽ ከጥፋትና ከውድቀት ይታደጋል

- ተግሳጽን የምትቀበሉ ከሆነ የተባረካችሁ ትሆናላችሁ፤ ትእዛዙን ተቀብላችሁ እግዚአብሔርን አክብራችኂልና ጥበብ፣ ባለጠግነትና ክብር ለእናንተ ይሆንላችኂል፡፡
- ተግሳጽን የምትንቁና የምትጠሉ ከሆነ ግን እናንተ ልታደርጉት የተዘጋጀውን በጎ ነገር አልሠራችሁምና ትጠፋላችሁ፡፡ ‹‹ተግሣጽን የሚጠብቅ በሕይወት መንገድ ይሄዳል ዘለፋን የሚተው ግን ይስታል፡፡›› *ምሳ 10:17፡፡*
- ተግሳጽን የምትቀበሉ በማስመሰል በተግባር ግን የምትጠሉት ለሆናችሁ ጠቢቡ ሰሎሞን የተናገረውን ሰነፍን ሰው ትመስላላችሁ፡፡ ‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ፡፡›› *ምሳ 1:7*፣ ‹‹ሰነፍ የአባቱን ተግሣጽ ይንቃል ዘለፋን የሚቀበል ግን አእምሮው የበዛ ነው፡፡›› *ምሳ 15:5*፣ ‹‹ተግሣጽን የሚወድድ እውቀትን ይወድዳል ዘለፋን የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው፡፡›› *ምሳ 12:1፡፡*
- በዚህም ወደ መንፈሳዊና ሞራላዊ ሞት ታመራላችሁ፡፡ ‹‹ክፉ መቅሠፍት መንገድን በተወ ሰው ላይ ይመጣል፥ ዘለፋንም የሚጠላ ይሞታል፡፡›› *ምሳ 15:10፡፡*
- እንግዲህ የሚገስጻችሁን ሳታቃልሉ ትወዱት ዘንድ እንመክራችኂለን፡፡ ‹‹ፌዘኛ ሰው የሚዘልፈውን አይወድድም፥ ወደ ጠቢባንም አይሄድም፡፡›› *ምሳ 15:12፡፡* ተብሎ ተጽፎልናልና፡፡
- የተወደዳችሁ ልጆች! ከወላጆቻችሁ ጋር ያለ ግኑኝነት ምን መምሰል እንዳለበት ታውቁና ተግሳጻቸውንም በመቀበላችሁ መንገዳችሁ በፊታችሁ የበራ ይሆን ዘንድ አመልክተናችኂል፤ ወላጆቻችሁ ለእናንተ ሊያደርጉት የሚገባውን አስቀድመን ወላጆቻችሁን አስረድተናቸዋልና፡፡

# <u>በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

6. ***<u>ዘወትር የሚሰጥ ፍቅር</u>***

- ልጆች ሁልጊዜ ከወላጆች ተቀባይ ቢሆኑም ወላጆችም ከነርሱ መቀበል የሚሹበት ጊዜያትም አሉ፡፡ በዓመታቱ ሁሉ ወላጆች ራሳቸውን ለልጆቻቸው መሥዋዕት አድርገው እንዳቀረቡ ሁሉ በእርጅናቸው ደግሞ የልጆቻቸውን ፍቅርና ክብካቤ ማግኘት የሚሹ ይሆናሉ፡፡ ይህም የሚከተሉትን መልኮች የሚይዝ ባለ ብዙ ኅብር ፍቅር ነው…

***<u>የፍቅር ቃላትን መጠቀም</u>***

- ልጆች ሆይ! ወላጆቻችሁ ምን ያህል ጊዜ አበረታተዋችኋል፣ አድንቀዋችኋል ወይም አመስግነዋችኋል? ወላጆች የፍቅር ቃላችሁን የሚፈልጉበት ጊዜ አለ፤ ይልቁንም በታመሙ ወይም ባረጁ ጊዜ እኛ ያስፈለገንንና ያደረጉልን የነበሩትን ሁሉ ይሹታል፡፡

***<u>ፍቅርን የምንሰጥበት ሁኔታ</u>***

- በምንታመምበት ጊዜ እናታችን ከጎናችን ሆና አባታችን ወደ ዶክተሩ ሲሮጥ የነበረበት ሁኔታ ይታወሰናል? ወላጆቻችን በሸመገሉ (ባረጁ) ጊዜስ እኛ ምን አደረግንላቸው? ከጎናቸው እንድንሆን ፈልገዋል? እኛስ ፍቅራችንን በመስጠት በልባቸው ደስታ እንዲሞላ አድርገናል? በኛ ልብ የዘሩትን (የተከሉትን) ፍቅር ማጨድ ችለዋል? ወይስ በነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹እግዚአብሔር ተናግሮአልና ሰማያት ስሙ፥ ምድርም አድምጪ ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም፥ እነርሱም አመጹብኝ፡፡በሬ የገዢውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀም፥ ሕዝቤም አላስተዋለም፡፡›› *<u>ኢሳ 1፡2-3፡፡</u>* በማለት የተነገረውን ቃል ደግመው እየተናገሩ ነው?

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

6. ***ዘወትር የሚሰጥ ፍቅር…***

***ፍቅርን የምንሰጥበት ሁኔታ***

- ወላጆቻችሁ የልደታችሁን ቀን ስንት ጊዜ አክብረውላችኋል? የጓደኞቻችሁንስ ልደት ስንት ጊዜ እንድታከብሩ አድርገዋችኋል? እናንተስ ስለነርሱ የልደት ቀናት ይገዳችኋል? ልጆቻችሁስ አብረዋቸው ያከብራሉ?
- ወላጆቻችሁ የገንዘብ እርዳታችሁን ሲፈልጉ ለእኛ እንዳደረጉልን ሳይጠይቁን እንሰጣቸዋለን? አንዳንድ ጊዜ ልጆቻቸው ከሌላው ሰው የተሻለ ነገር እንዲኖራቸው፣ ከጓደኞቻቸውም እንዳያንሱ ብለው ለራሳቸው ከሚያስፈልጋቸው  አጉድለው የሚያደርጉ ወላጆች ይገጥሙናል፡፡

***መልካም ዜናን ማሰማት***

- ልጆች ለወላጆቻቸው ችግሮቻቸውን፣ ሕመማቸውን ወይም ፍላጎታቸውን የመናገር ዝንባሌ አላቸው፡፡ ነገር ግን ውጤታማነታችንን፣ ዕድገታችንን የልጆቻችንን ዕድገት… ስለምን አንነግራቸውም?
- ወላጆች በእርጅናቸው ክፉ ወሬዎችን ማስተናገድ የሚያቅታቸው ሲሆን፤ ይልቁንም ‹‹የቀዘቀዘ ውኃ ለተጠማች ነፍስ ደስ እንደሚያሰኝ፥ ከሩቅ አገር የመጣ መልካም ምስራች እንዲሁ ነው፡፡›› *ምሳ 25፡25፡፡* በማለት ጠቢቡ ሰሎሞን እንደተናገረው መልካሙን ዜና ለመስማት ግን ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

6. ***ዘወትር የሚሰጥ ፍቅር…***

***ፍቅርን የምንሰጥበት ሁኔታ***

- *ያዕቆብ የልጁ ዮሴፍን ሞት ሲሰማ ያደረገውን ታስታውሳላችሁ? «ያዕቆብም ልብሱን ቀደደ፥ በወገቡም ማቅ ታጥቆ ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ።ወንዶች ልጆቹና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት ተነሡ መጽናናትን እንቢ አለ፥ እንዲህም አለ። ወደ ልጄ ወደ ሙታን ስፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ። አባቱም ስለ እርሱ አለቀሰ።»* ***ዘፍጥ 37፡34-25።***
- ስለዮሴፍ መልካሙን ዜና ሲሰማ ደግሞ ‹‹እነርሱም ዮሴፍ የነገራቸውን ነገር ሁሉ ነገሩት እርሱን ያነሡት ዘንድ ዮሴፍ የሰደዳቸውን ሰረገሎች ባየ ጊዜ የአባታቸው የያዕቆብ የነፍሱ ሕይወት ታደሰች።›› ***ዘፍጥ 45፡27።***
- ካህኑ ዔሊ የታቦተ ጽዮንን መማረክና የሁለቱ ልጆቹን ሞት ሲሰማ ‹‹ወሬኛውም መልሶ፦ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ ግድያ ሆኖአል፥ ሁለቱም ልጆችህ አፍኒንና ፊንሐስ ሞተዋል የእግዚአብሔርም ታቦት ተማርካለች አለ።ሰውዮውም ስለ እግዚአብሔር ታቦት በተናገረ ጊዜ ዔሊ በበሩ አጠገብ ካለው ከወንበሩ ወደቀ እርሱ ሽምግሎ ደንግዞም ነበርና አንገቱ ተሰብሮ ሞተ። እርሱም በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት ፈራጅ ነበረ።›› ***ቀዳ ሳሙ 4፡17-18።***
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በባሕር እንዳለ፡ መረጋጋትን እስክታገኙ ድረስ ትዋኙበት ዘንድ ወላጃቻችሁ እንደሰጡአችሁ የፍቅር እንጥብጣቢ አድርጋችሁ መልሳችሁ ፍቅርን ለወላጆቻችሁ ስጡ።

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## *ወንድማዊ ፍቅር*

- *መሥዋዕትነት ስለሚሻው የትዳር ፍቅር፣ ጥበብና ደግነት ስላለው የወላጅ ፍቅር እንዲሁም ራስን መስጠትን ወይም መታዘዝን ስለተመለከትንበት ልጆች ለወላጆቻቸው ሊኖራቸው ስለሚገባው ፍቅር ተማርን፡፡ በመቀጠል የምንመለከተው ስለወንድምነት ፍቅር ነው፡፡*
- *ማንኛውንም ሰው፣ ዘመዶቻችንን፣ ጠላታችንን ሳይቀር እንደራሳችን አድርገን እንድንወድ ተጠይቀናል፡፡ ታዲያ ከወንድሞቻችንና ከእህቶቻችን ጋር ያለን ግኑኙነት ምን ይመስላል? ጠቢቡ ሰሎሞን «የተበደለ ወንድም እንደ ጸናች ከተማ ጽኑ ነው ክርክራቸውም እንደ ግንብ ብረት ነው፡፡» **ምሳ 18፡19**፣ «ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳል ወንድምም ለመከራ ይወለዳል፡፡» **ምሳ 17፡17፡፡***

## *ወንድማዊ ፍቅር ራስ ወዳድ አይደለም*

- *ወንድምና እህቶቻችንን ከራሳችን አብልጠን መሥዋዕት በመሆን በህይወታቸው የተመቸ ነገር ይኖራቸው ዘንድ እንድንወዳቸው ታዘናል፡፡*
- *የልበ አምላክ ዳዊትን ሕይወት ብንመረምር ራስ ወዳድነት የሌለበት ንጹሕ ወንድማዊ ፍቅር ምን እንደሚመስል እንማርበታለን፡፡*
- *አባቱ እሴይ ጦርነት በሚካሄድበት ሥፍራ የሚገኙ ወንድሞቹን ይጎበኛቸው ዘንድ ሲልከው በማለዳ ተነስቶ ምግብ ይዞላቸው የራሱን ሕይወት ለአደጋ ሰጥቶ ሄደ፡፡ **ቀዳ ሳሙ 17፡፡** «ዳዊትም ማልዶ ተነሣ፥ በጎቹንም ለጠባቂ ተወ፥ እሴይም ያዘዘውን ይዞ ሄደ ጭፍራውም ተሰልፎ ሲወጣ ለሰልፍም ሲጮኽ በሰረገሎች ወደ ተከበበው ሰፈር መጣ፡፡» **ቀዳ ሳሙ 17፡20፡፡***

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ወንድማዊ ፍቅር…***

- ለወንድሞቹ ክፋት የፍቅር ምላሽ የሰጠውን የዮሴፍንም ፍቅር እንዲሁ እንመለከታለን፡፡ «እስራኤልም ዮሴፍን፦ ወንድሞችህ በሴኬም በጎችን የሚጠብቁ አይደሉምን? ወደ እነርሱ እልክህ ዘንድ ና አለው:: እርሱም፦ እነሆኝ አለው::» ***ዘፍጥ 37፡13፡፡***
- በፍቅርም ፈጥኖ ወደ ወንድሞቹ በመሄድ መንገድ እስኪጠፋው ድረስ ፈለጋቸው፡፡ «እነሆም በምድረ በዳ ሲቅበዘበዝ ሳለ አንድ ሰው አገኘው ሰውዮውም:: ምን ትፈልጋለህ? ብሎ ጠየቀው::» ***ዘፍጥ 37፡15፡፡*** እንደተባለው ወንድሞቹን እስኪያገኛቸው ድረስ ጸንቶ ፈለጋቸው፡፡
- እኛም ይህን በመሰለ ፍቅር ልንኖር ይጠበቅብናል፡፡ ውርስን በተመለከተ ክርክር ሲገጥመን የበለጠ የሚያስፈልገውን በመለየት በወንድማዊ ፍቅር ምላሽ መስጠት ወይም መስማማት ይጠበቅብናል፡፡
- እንዲህ ያለውም ፍቅር ያላቸውን ሁሉ ወንድምና እህቶች ሁሉ በፍቅር እንዲካፈሉ ይረዳቸዋል፡፡
- አብርሃም ለሎጥ ያሳየውም ይኸንኑ ፍቅር ነው፡፡ «አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ::ምድር ሁሉ በፊትህ አይደለችምን? ከእኔ ትለይ ዘንድ እለምንሃለሁ አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ አንተም ቀኙን ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ::» ***ዘፍጥ 13፡8-9፡፡***
- ሎጥ አስቀድሞ ይመርጥ ዘንድ ዕድል ተሰጠው፡፡ ሎጥም «ሎጥም ዓይኑን አነሣ፥ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ ዞዓር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብፅ ምድር አምሳል ነበረ::» ***ዘፍጥ 13፡10፡፡*** እንደተባለው ከአብርሃም ቀድሞ ሣር የበዛበትን ለም የሆነውን የሰዶምን ምድር መረጠ፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*ወንድማዊ ፍቅር…*

- ሎጥም በዚህ ምርጫው ልጆቹንና ሚስቱንም ሳይቀር አጣ። ራስ ወዳድነትን ከሕይወቱ በማራቅ በፍቅር የተገኘው አብርሃም ግን እጅግ ባለጠጋ ሆነ፤ ይህንም አገልጋዩ ‹‹እርሱም አለ፦ እኔ የአብርሃም ሎሌ ነኝ።እግዚአብሔርም ጌታዬን እጅግ ባረከው፥ አገነነውም በጎችንና ላሞችን፥ ብርንም፥ ወርቅንም፥ ወንዶች ባሪያዎችንና ሴቶች ባሪያዎችን፥ ግመሎችንም አህዮችንም ሰጠው።›› ***ዘፍጥ 34፡24-25።*** በማለት መሰከረ።
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! የወንድማዊ ፍቅር በልብ ውስጥ በጥልቀት ከተተከለ ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች እንዴት ያለ ፍሬን እንደሚያፈራ ተመለከታችሁ?

*በወንድማዊ ፍቅር መቀናናት የለም*

- ቃየን ፍቅርን አጥቶ በወንድሙ ላይ በክፋትና በቅንዓት ተነሳስቶ የገዛ ወንድሙን አቤልን ገድሎታል። ቃየን ሥጋዊ ቅንዓት የገዛው ሰው ነበር። ‹‹አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።›› ***ዘፍጥ 4፡4-5።***
- ሥጋዊ ቅንዓቱም ወንድሙን ለመግደል አበቃው። እግዚአብሔርም ‹‹አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።›› ***ዘፍጥ 4፡11።***
- ምድርም በርስዋ ላይ ሥልጣን እስኪያጣ ድረስ ተቃወመችው። ‹‹ምድርንም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ ኃይልዋን አትሰጥህም በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ።›› ***ዘፍጥ 4፡12።***

# <u>በቤታችን ያለች ቤት ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

## <u>*ወንድማዊ ፍቅር…*</u>

- ይኽን የመሰለው ነገር በዮሴፍ ወንድሞችም ደርሶባቸዋል፡፡ ‹‹እነርሱም በሩቅ ሳለ አዩት፥ ወደ እነርሱም ገና ሳይቀርብ ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ፡፡አንዱም ለአንዱ እንዲህ አለው፦ ያ ባለ ሕልም ይኸው መጣ፡፡አሁንም ኑ፥ እንግደለውና በአንድ ጕድጓድ ውስጥ እንጣለው፡፡ ክፉ አውሬም በላው እንላለን ከሕልሞቹም የሚሆነውን እናያለን፡፡›› <u>*ዘፍጥ 37፡18-20፡፡*</u>
- ወንድም ወይም እህቶቻችን ስኬታማ በመሆናቸውም፣ በትምህርታቸው፣ ወይም ከእኛ ይልቅ ትኩረት በማግኘታቸውም የተነሳ ከክፋት የተነሳ ለሥጋዊ ቅንዓት ልቦናችንን አሳልፈን መስጠት አይገባንም፡፡
- እነርሱ በዚህ ዓለም ሀብት ባለጠጎች ቢሆኑ እኛ በመንፈሳዊ ሕይወት ለመበልጸግ፣ እነርሱ በዚህ ምድር ሰፊ ቦታ ቢኖራቸው እኛ ሰማያዊ ርስትን ለማግኘት በእግዚአብሔር ጠንክረን በማመን ለመኖር ጥረት እናድርግ፡፡
- እነርሱ በሰዎች ትኩረት አግኝተው እንደሆነ እኛ ለዘላለሙ በማይለወጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ትኩረት እናገኝ ዘንድ፣ እነርሱ በዚህ ዓለም አጊጠው እንደሆነ እኛ ከሁሉ በሚልቀው ሰማያዊ ጌጥ (መንፈሳዊነት) በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት አሸብርቀን ለመገኘት እንጣጣር፡፡ <u>*ቆላ ጸጥ 3፡4፡፡*</u>
- ስለዚህ በልቦናችን *ሥጋዊ* ቅናት *ሥፍራ* አያግኝ! ይልቁኑ በእኛ በኩል ሌሎቹን ከመጉዳቱ በፊት እናርቀው፡፡

## <u>*ወንድማዊ ፍቅር ክፋትን አያደርግም*</u>

- ወንድምና እህታችን ያለፍቅር፣ እየሰደቡ ወይም እያዋረዱን፣ ለፍቅራችን በጭካኔ (በጥላቻ) ሲመልሱልን ምን ይሰማናል? ለነርሱ ያለን ፍቅር እንደጸና ይቀጥላል? ወይስ ክፋትና ቅንዓት ወደ ልቦናችን ገብተው ለእነርሱ ያለንን አመለካከት ያበላሹታል?

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ወንድማዊ ፍቅር ክፋትን አያደርግም…***

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በእኛ የሚከፉብንና የሚጨክኑብን ሰዎች የፍቅራችን ልክና ደረጃ መለኪያ ናቸው፡፡ በእውነት ወንድማዊ ፍቅር ክፋት የለበትም ለሚጎዱትም ሳይቀር ፍቅርን ይሰጣል፡፡
- ለዮሴፍ ወንድሞች ከወንድማቸው የሚበልጥባቸው ገንዘብ ነበር፡፡ እንደ ጻድቁ ዮሴፍ ያለ ሰው ሰው ደግሞ ከክፋትና ከቅንዓት ርቆ ሊገድሉት ቢፈልጉ፣ እንደባሪያ ቢሸጡት፣ ከፍቅሩ የተነሳ ወንድሞቹን ይፈልጋል፡፡
- ዮሴፍም በልቡ የነበረው ቁስል ለወንድሞቹ የነበረውን ፍቅር አልለወጠውም፡፡ በልቡ የሞላው ፍቅር ሥነ ልቦናዊ ችግሩን የሚፈታለት መድኃኒት ነበር፡፡ ዮሴፍን የወደደው እግዚአብሔርም ለወንድሞቹ ባሳየው ፍቅር ግብጽን ከረሃብ ለማዳን መሣሪያ ሊያደርገው ዮሴፍን እድሜ ሰጠው፡፡
- ወንድሞቹንም ሲገናኝ ክፋትን በቅንዓታቸው ካደረጉበት በላይ በሆነው ፍቅሩ ከወንድሞቹ ጋር ለብቻው የሚገናኝበት ሥፍራ አዘጋጅቶ ዓይኑ በእንባ እየታጠበ አለቀሰ፡፡ ያለቀሰውም ከፍቅሩ እንጂ ለበቀል ከነበረው ፍላጎት የተነሳ አይደለም፡፡ ‹‹ወንድሞቹን ሁሉ ሳማቸው፥ በእነርሱም ላይ አለቀሰ ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር ተጫወቱ፡፡›› ***ዘፍጥ 45፡15፡፡***
- በማስከተልም ወንድሞቹን ‹‹ እኔ ዮሴፍ ነኝ አባቴ እስከ አሁን በሕይወቱ ነውን? አለ፡፡ ወንድሞቹም ይመልሱለት ዘንድ አልቻሉም፥ በፊቱ ደንግጠው ነበርና፡፡›› ***ዘፍጥ 45፡3፡፡***
- በእጁ ወድቀዋል፣ ከነርሱ ይልቅ ብሩቱ ሆኖ ሊበቀላቸው የሚችልበት አቅም አለውና ዮሴፍ መሆኑንም ሲያውቁ ደነገጡ፡፡ ወነወድሞቹ የዮሴፍም ልብ በእጁ ሥር ከነበረው ከግብጻውያን ኃይል ሁሉ በላይ በሆነው በፍቅር የተሞላ መሆኑን አላወቁም ነበር፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ወንድማዊ ፍቅር ክፋትን አያደርግም…***

- ዮሴፍም ስሜታቸውን ለማወቅ ፈጣን ነበር፡፡ ከፍርሃታቸውና ከጭንቀታቸውም ሊገላግላቸው ወዶ ወደ እኔ ቅረቡ ‹‹አሁንም ወደዚህ ስለ ሸጣችሁኝ አትዘኑ፥ አትቈርቈሩም እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና፡፡›› ***ዘፍጥ 45፡5፡፡*** አላቸው፡፡
- ዮሴፍ ‹‹እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና፡፡… አሁንም እናንተ ወደዚህ የላካችሁኝ አይደላችሁም፥ እግዚአብሔር ላከኝ እንጂ ለፈርዖንም እንደ አባት አደረገኝ፥ በቤቱም ሁሉ ላይ ጌታ፥ በግብፅ ምድርም ሁሉ ላይ አለቃ አደረገኝ፡፡›› ***ዘፍጥ 45፡8፡፡*** በማለት በፍቅር ተቀብሎ ለእስማኤላውያን መሸጡ ለበጎ መሆኑን ነገራቸው እንጂ አልተቆጣቸውም፣ አልተበቀላቸውምም፡፡
- በምድር ላይ ራብ በሆነ ጊዜም በግብጽ ምድር በጥጋብ እንዲቆዩ በመፍቀድ፣ ሲሄዱም በቂ እህል ጭኖ በመስጠት ያን እርሱን ወደ ጉድጓድ የጣሉበትና የሸጡበት ጊዜ ማለፉንና እርሱም ያን ሁሉ መርሳቱን አስረዳቸው፡፡
- ዮሴፍ እግዚአብሔር ያደረገለትን ፈጽሞ አልረሳም፡፡ በፍቅር የተሞላው ልቦናውም በወንድሞቹ የተነሳ በፍጹም ሕመም አልተሰማውም፡፡
- የዮሴፍን ፍቅር በመመልከት በእኛ ልብ ያለውን ፍቅር እስኪ እንመዝነው፡፡ በልባችን ያለው እውነተኛ ፍቅር ነው? ከክፋትና ከበቀል የራቀ ከሆነ አዎ እውነተኛ ፍቅር ነው፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ወንድማዊ ፍቅር ክፋትን አያደርግም…***

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ክፋትና በቀል ይርቅልን ዘንድ ከወደድን፡-
  1. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየውን ፍቅር እንመልከት፡፡ ግርፋቱንና የሰውን ክፋት በመታገስ፣ ለኃጢአተኞች በመስቀል በመሞት፣ የሰቀሉትን ይቅር ብሎአልና፡፡
  2. ክፋትን ሁሉ ያሸነፈ ፍቅራቸው እንዴት እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንደ ጻድቅ ዮሴፍ ካሉ ቅዱሳንን ሕይወት እንመርምር፡፡
  3. ሰዎች በእኛ ካደረጉት ይልቅ እግዚአብሔር በእኛ ያደረገውን፣ የሰውን ክፋት ሳይሆን ክፉውን ወደ በጎ የሚለውጠውን የእግዚአብሔርን ፍቅር እናስተውል - እናስታውስ፡፡
  4. በሌሎች ሰዎች በፍቅር የተደረገልንን በጎውን ነገር ሁሉ በማሰብ፡ በስህተታቸውና በድካማቸው ጊዜ ሁሉ በጎነታቸውን በዓይናችን ፊት እናኑር፡፡ ስህተታቸውንና ጥፋታቸውን እንረሳ ዘንድ ፍቅራቸውን እናስብ፡፡
  5. ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፡፡›› ***ቀዳ ዮሐ 3፡14፡፡*** በማለት የጻፈልንና ከእናንተ ለሌሎች የሚጠየቀውን፣ ከሞት ወደሕይወት ያሸጋገረንን የእግዚአብሔርን ፍቅር እናስብ፡፡
  6. ‹‹ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፡፡›› ***ቀዳ ዮሐ 3፡14፡፡*** በማለት መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረን ፍቅር የሌለው በሞት እንደሚኖር ልብ ብለን እናስተውል፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ወደ ተዘጋጀልን የፍቅር ሠረገላ በፍጥነት ወጥተን ክፋትን ሁሉ በማሸነፍ በደስታ ወደ ዘላለማዊቱ መንግሥት እንደርስ ዘንድ እንሽቀዳደም!!! ለዚሁ የበቃንም ያድርገን! አሜን!!!

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org